Washington State Health Care Authority

# የMedicare ቁጠባ ፕሮግራሞች በMedicare ላይ ገንዘብ ይቆጥቡ

## በዓመት ከ$2,400 ዶላር በላይ

## ገንዘብዎን ወደ ማህበራዊ ዋስትና ቼክዎ ይመልሱ!

### ስለMedicare የቁጠባ መርሀግብር

በዋሸንግተን ስቴት ውስጥ አራት ፕሮግራሞች አሉ፡

**ፕሮግራም 1**
**ብቁ የMedicare ተጠቃሚ (QMB) ፕሮግራም**

- የክፍል A እና የክፍል B ክፍያዎችን ይከፍላል
- ተቀናሽ ክፍያዎችን ይከፍላል
- ከመድኃኒት ማዘዣዎች በስተቀር የጋራ ክፍያዎችን ይከፍላል

**ፕሮግራም 2**
**የተወሰነ የዝቅተኛ ገቢ Medicare ተጠቃሚ (SLMB)**

- የክፍል B ፕሪሚይም ይከፍላል

**ፕሮግራም 3**
**ብቁ የተናጠል ፕሮግራም (QI-1)**

- የክፍል B ፕሪሚይም ይከፍላል

**ፕሮግራም 4**
**ብቁ የሆነ የአካል ጉዳተኛ ሠራተኛ ግለሰብ (QDWI)***

- የክፍል A ፕሪሚይም ይከፍላል

### ብቁ እንደሆኑ ይወቁ

ይህንን የግል ዎርክሺት ይጠቀሙ፡፡

ለMedicare ቁጠባ ፕሮግራም ብቁ መሆን አለመሆንዎን ለማወቅ ከታች ያሉትን ቀላል ደረጃዎች ይከተሉና አጠቃላይ ድምርን ከታች ካለው ሰንጠረዥ ጋር ያወዳድሩ፡፡

1. **ጠቅላላ** ወርሃዊ የቤተሰብ ገቢዎን ይፃፉ: $______________
2. ዶላር $20 ይቀንሱ (በአንድ ቤተሰብ አንድ ቅናሽ): $______________
3. ***ጠቅላላ ገቢ:*** $______________
4. ወርሃዊ ገቢዎ ከታች ባለው ገበታ ላይ ካሉት ደረጃዎች ውስጥ በማንኛውም ላይ ወይም ከዚያ በታች ከሆነ፣ ከMedicare ቁጠባ ፕሮግራሞች ውስጥ ለአንዱ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

### የMedicare ቁጠባ ፕሮግራሞች የገቢ ደረጃዎች

| የMedicare ፕሮግራም ዓይነት | ወርሃዊ ገቢ (ግለሰብ) | ወርሃዊ ገቢ (ጥንዶች) |
|---|---|---|
| ፕሮግራም 1 QMB | እስከ $1,483 | እስከ $2,004 |
| ፕሮግራም 2 SLMB | እስከ $1,616 | እስከ $2,185 |
| ፕሮግራም 3 QI-1 | እስከ $1,855 | እስከ $2,510 |
| ፕሮግራም 4 QDWI* | እስከ $2,680 | እስከ $3,628 |

***ከ4/1/2026 ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል**

ለሚሰሩት የአካል ጉዳተኞች የQDWI ፕሮግራም ልዩ የገቢ ቅነሳዎች ስላሉት ለዚህ ፕሮግራም ብቁነትን ለመወሰን እርዳታ መጠየቅ ያስፈልግዎታል፡፡

## እንዴት ማመልከት እችላለሁ?

*ቀላል ነው! ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ አንዱን ያነጋግሩ፡*

- በአቅራቢያዎ የሚገኝ CSO ያግኙ፡ **dshs.wa.gov/office-locations**
- በኢንተርኔት፣ ወደዚህ ድረ ገጽ ይሂዱ፡ **washingtonconnection.org/home/**
- የጤና እንክብካቤ ባለስልጣኑን በ1-800-562-3022፣ የውስጥ መስመር 16129 ማመልከቻ እንዲላክልዎት ያነጋግሩ።
- የስቴት አቀፍ የጤና ኢንሹራንስ ጥቅማጥቅም አማካሪ (SHIBA)ን በ1-800-562-6900 ያግኙ እና ከአካባቢዎ የSHIBA ቢሮ ጋር እንዲገናኙ ይጠይቁ።
- ለMedicare ክፍል D ተጨማሪ እገዛ

  የማህበራዊ ዋስትና አስተዳደርን በ1-800-772-1213 ያግኙ ወይም የሚከተለውን ይጎብኙ፡ **ssa.gov/medicare/part-d-extra-help**

## የMedicare ተጠቃሚ ከሆኑ

በዓመት ከ$2,200 ዶላር በላይ ሊቆጥብልዎት የሚችል ፕሮግራም ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። የMedicare ቁጠባ ፕሮግራሞች የMedicare ፕሪሚየሞችን፣ ተቀናሽ ክፍያዎችን እና ሌሎች ከMedicare ጋር የተያያዙ ወጪዎችን በመክፈል ብቁ የሆኑ ሰዎችን ይረዳሉ። መደበኛውን Medicare ወይም በMedicare የሚተዳደር የእንክብካቤ እቅድ መጠቀም ይችላሉ።

## ማመልክት ቀላል ነው።

ለመረጃ እና እገዛ ዛሬውኑ ይደውሉ - ገንዘብ ወደኪስዎት መልሰው ይከታሉ!

## ምን ዓይነት ወጪዎች ናቸው የሚሸፈኑት?

Medicare የቁጠባ መርሀግብር የሚከተሉትን ይሸፍናል፡

- ክፍል A ፕሪሚየሞች
- ክፍል B ፕሪሚየሮች
- Medicare የጥምረት መድህን
- Medicare ተቀናሾች

## ብቁ መሆኔን እንዴት ማወቅ እችላለሁ?

በሺዎች የሚቆጠሩ በዋሽንግን የሚኖሩ ሰዎች ለMedicare የቁጠባ ፕሮግራም ብቁ ይሆናሉ። ብቁ እንደሆኑ ለማወቅ በዚህ በራሪ ወረቀት ላይ የሚገኘውን የገቢ ሰንጠረዥ ይመልከቱ። ወርሃዊ ገቢዎ ከላይ ባለው ገበታ ላይ ካሉት ደረጃዎች ውስጥ ወይም በታች ከሆነ፣ ለMedicare ቁጠባ ፕሮግራሞች ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

## እነዚህ ጥቅሞች ንብረቴ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ?

አይ፣ ለMedicare የቁጠባ መርሀግብር ከንብረት ላይ ተመላሽ ማድረግ የለም።

ለጊዜው የሚቆዩበትን ቦታ ከፈለጉ፣ ወይም ሰነዱን በሌላ ፎርማት ማግኘት ከፈለጉ እባክዎትን ወደ 1-800-562-3022 (TRS: 711) ይደውሉ



